# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 198 የካቲት 22 2004 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግንቦት 7፡ ይህ ትውልድ ከደረሰበትን ታሪካዊ ውርደት መውጣት አለበት ብሎ በጽኑ ያምናል። መንገዱን አያቶቻችን ከዛሬ 116 ዓመት በፊት በአድዋ ጦርነትና ድል አሳይተውናል። መንገዱ አርበኝነት ነው፤ ተጋድሎ ነው፤ ትግል ነው።

የአያቶቻችን የልጅ ልጆች፤ የአባቶቻችንና የእናቶቻችን ልጆች ለመሆን እንድንችል ትግሉን እንቀላቀል፣ አለበለዚያ ግን በባርነት እየኖሩ በነሱ ተጋድሎ መኩራራት አሳፋሪ ነው ።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## መቶ አስራ ስድስተኛው የአድዋ ድል መታሰቢያ በዓል ትላንት ተከበረ፤ ህዝብ ግን “የኛ ዘመን አድዋ መቸ ነው የሚመጣው?” ብሎ እየጠየቀ ነው

አባቶቻችንና እናቶቻችን የኢጣሊያ ወራሪን ድል መትተው አገራችንን የነፃነት ተምሳሌት ያደረጉበት የአድዋ ድል ለ116ኛ ጊዜ ታስቦ ዋለ። የአድዋ ድል ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካ፤ ከዚያም አልፎ የጥቁር ህዝብ ሁሉ መመኪያ ሆኖ ቆይቷል። የአድዋ ድል ለነፃነታቸው ለሚታገሉ ህዝቦች ሁሉ አርአያ ሆኗል።

የአውሮፓ ወራሪ ኃይል በአፍሪካ ምድር ውስጥ ሽንፈት ሲደርስበት አድዋ የመጀመሪያው ነው። በመሣሪያ ብዛትም ሆነ ጥራት ፈጽሞ የማይቀራረቡ ባላንጣዎች ተፋልመው በጣልያኖች ዓይን ደካማ የነበረው የኢትዮጵያ ሠራዊት በጦር ሜዳ ውስጥ ጀግንነቱን አስመሰከረ። የአባቶቻችንና የእናቶቻችንን ድል የምናከብረው እኛ ራሳችን በወያኔ ባርነት ውስጥ ተዘፍቀን መሆኑ በርካታ ኢትዮጵያዊያንን ያሳዘነ ጉዳይ እንደሆነ ያሰባሰብነው መረጃ ያመለክታል።

አስቻለው የተባለው ወጣት ፌስ ቡክ በተሰኘው ድረገጽ እንዲህ የሚል ጽሁፍ ትቷል “የአድዋ ድል ክብር፤ በአድዋ ከተማ ተወላጅ የባንዳ ልጅ መለስ ዜናዊ መርከሱ አያሳዝንም? ጎበዝ!! ይህ ትውልድ ሌላ አድዋ ያስፈልገዋል፤ በአስቸኳይ!!!” ይላል

መቅደስ የተባለች ወጣት ደግሞ “ ዛሬ የአድዋ ድል መታሰቢያ ቀን ነው!!! አድዋ በእኛ ዘመን፤ አድዋ በእኔ ሕይወት የሚሆነው መቼ ነው???” ስትል ጠይቃለች።

በክሪ የተባለ ሌላ ኢትዮጵያዊ ደግሞ “ስለ አባቶቻችን ድል እያወራን ስንት ዘመን እንገዛለን?” ሲል ጠይቋል።

ንቅናቄያችን በቁጥር 198 “የአድዋ ድልን ኩራታችን፤ በወያኔ መገዛት ውርደታችን ነው!!” በሚል ርዕስ ያወጣው ርዕሰ አንቀጽ ይህንኑ የተመለከተ ነው። ግንቦት 7 በዚህ መግለጫው ንቅናቄው አባቶቻችንና እናቶቻችን ለነፃነትና ለክብር በነበራቸው ቀናዒነት የሚኮራ ቢሆንም እነሱ በተጋድሎ ያስቀሯትን አገር ለባንዶች ማስረከባችን ያሳፍረናል ብሏል። በመግለጫው መጨረሻም የአያቶቻችን የልጅ ልጆች፤ የአባቶቻችንና የእናቶቻችን ልጆች ለመሆን እንድንችል ትግሉን እንቀላቀል፣ አለበለዚያ ግን በባርነት እየኖሩ በነሱ ተጋድሎ መኩራራት አሳፋሪ ነው ብሏል።

## የሙስሊም ማኅበረሰብ ያቀረባቸው የመብት ጥያቄዎች አልተመለሱም፤ ትግሉ ተጠናክሮ ቀጥሏል

የኢትዮጵያ ሙስሊም ማኅበረሰብ

1ኛ. የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በእስልምና ሃይማኖት ጣልቃ በመግባት የአህባሽ አስተምህሮት ተከታዮች ጥሩዎች፤ ሌሎች ሞስሊሞች ክፉዎችና ፀረ ሰላሞች እያለ መከፋፈሉን እንዲያቆም እና ከሃይማኖት ላይ እጁን እንዲሰበስብ፤

2ኛ. በጀማው የተጠላው ሆኖም ግን በወያኔ የተወደደው የኢትዮጵያ እስላማዊ ምክር ቤት (መጅሊስ) አመራሮች ሥልጣን እንዲለቁ፤ እና

3ኛ. አወሊያ የትምህርት ተቋም ከወያኔ ተጽዕኖ ነፃ እንዲሰራ።

የሚሉ ጥያቄዎችን አቅርበው ትግል ከጀመሩ ስምንት ሳምንታት ተቆጥረዋል። በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ ከወያኔ በኩል ከዛቻና ማስፈራሪያ በቀር የመፍትሄ ሃሳብ አልተገኘም። በዚህም ምክንያት የተቃውሞ ድምጽ በየጁምዓው ይሰማል።

ለወያኔ የመብት ጉዳይ የሚያነሳ ሁሉ አሸባሪ ነው። በዚህም መሠረት አንድ ጊዜ “አሸባሪዎችን ይዣለሁ፤” ሌላ ጊዜ “አዲስ አበባ ውስጥ ሃይማኖትን አስታክኮ ከሚሰማው ውዥንብር ራሳችሁን አግልሉ” እያለ ህዝቡን ሲያሸብር ከርሟል።

ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ያነሷቸውን የመብት ጥያቄዎች አንግበዉ ትግላቸውን አጠናክረው ቀጥለዋል። በየሳምንቱ ከጁምአ ጸሎት በሁዋላ የሚደረገው ተቃውሞ እያየለ መጥቶ ባለፈው ሳምንት አርብ ከ120 ሺህ በላይ የሚሆኑ አማኞች ለ7 ሰዓታት የቆየ ተቃውሞ አድርገዋል። ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ጥያቄያቸው ተገቢውን ምላሽ እስኪያገኝ ድረስም፤ ተቃውሟቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ አስታውቀዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ጥምረት ለነጻነት፣ ለእኩልነትና ለፍትህ ከሚያዘጋጃቸው ስብሰባዎች መካከል ሁለተኛው በሂውስተን ቴክሳስ ተካሄደ

በዚሁ ስብሰባ ላይ የግንቦት 7 ምክትል ሊቀመንበር የሆኑት አቶ አበበ ቦጋለ፣ የኦነግ የስራ አስፈጻሚ አባልና የድርጅት ጉዳይ ሀላፊ የሆኑት አቶ አዴሳ ቦሩ እና ተዋቂው አርቲስትና የሰብአዊ መብት ተሚጋቹ ታማኝ በየነ በእንግድነት ተገኝተዋል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ ምክትል ሊቀመንበር የሆኑት አቶ አበበ ቦጋል ጥምረት ለነጻነት፤ ለፍትሃና ለእኩልነት በጄነራል ከማል ገልቹ ከሚመራው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጋር ባለፈው ሳምንት ዋሽንግተን ዲሲ ላይ ባደረገው የመጀመሪያው የጋራ ስብሰባ ወቅት “አሁን አገራችንን ከተዘፈቀችበት ችግር ለማውጣት ጥሩ ፖለቲከኛ መሆን ብቻውን በቂ አይደለም” በማለት የተናገሩትን የጥምረት ሊቀመንበርን ንግግር ጠቅሰው የአገራችንን ዘርፈ ብዙ ችግር የተረዳ ሁሉንም በሆደሰፊነትና በአርቆ አሳቢነት ማሰባሰብ የሚችል ባለራዕይ መሪ የሚያስፈልጉንን ያህል፤ እንዲህ አይነት ባለ ራዕይ መሪ ለመፍጠር የሚችልና የገባንበትን ችግር በሚገባ ተረድቶ ከችግሩ ለመውጣት የሚደረገወን ትግል በሞራሉ፤ በገንዘቡና በዕውቀቱ ለመርዳት ዝግጁ የሆነ ህብረተሰብም መኖር ወሳኝነት አለው ብለዋል። በመቀጠልም በተለይ በትምህርቱ ፤ በገንዘቡና ነጻነት የሰፍነበት ህብረተሰብ ውስጥ ለመኖር ባገኘው ዕድል የተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኘው የዲያስፖራ ኮሚኒቲ እንዲህ አይነቱን ህብረተሰብ ለመፍጠር ግንባር ቀደም ምሳሌና አረአያ የመሆን ሃላፊነት እንዳለበት አስገንዝበው፤ በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ፤ አገር እየፈረሰች ዜጎች እየተፈናቀሉ ከዳር ቆሞ የሚመለከት ማንኛውም ሰው ታሪክ የፈጠረለትን አገር የማዳን ሃላፊነቱን ለመወጣት ዛሬውኑ ትግሉን ካልተቀላቀለ ከሂሊናና ከታሪክ ፍርድ አያመልጥም ሲሉ አሳስበዋል። በመጨረሻም ሁሉም የአገሪቱ ዜጋ ከገባንበት እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለመውጣት የራሱን አስተዋጾ እንዲወጣ የትግል ጥሪ አቅርበዋል።

በጄኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦነግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የድርጅት ጉዳይ ሀላፊ የሆኑት አቶ አዴሳ ቦሩ፤ ግንባራቸው አሁን የወሰደው የፕሮግራም ለውጥ በወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ከፍተኛ ስቃይ እየተፈጸመበት ያለውን የኦሮሞ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ተመሳሳይ ስቆቃ የሚፈጸምበትን መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ካለበት ስቃይ ሊገላግል የሚችል እርማጃ ነው ብለዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ ገበሬው እንዳያምጽበት በእርከን ሥራ ወጥሮ የያዘው መሆኑ ተገለፀ

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ባጠናቀረው ዘገባ መሰረት የደቡብ፣ አማራ እና ድሬዳዋ ገበሬዎችን ህዝብን ለመቆጣጠር ወያኔ በቀየሰው አንድ ለአምስት አደረጃጀት በመጠቀም ፣ አርሶአደሩን እና በተለያዩ ወረዳዎች የሚኖሩ ዜጎችን በግዳጅ በሳምንት ለሶስት ቀናት የእርከን ስራ እንዲሰሩ እያደረገ ነው።

አርሶ አደረች ለኢሳት እንደገለጹት በቦረና ዞን በተለያዩ ቀበሌዎች በርካታ ሰዎች በእርከን ሥራ ሰበብ ታስረዋል። የእርከን ሥራ እየተሰራ ያለው እርከን በማያስፈልግበት ቦታ ጭምር መሆኑ ገበሬዎችን እያበሳጨ መሆኑ ዘገባው ያመለክታል።

አንድ ስማቸው እንዳይገለጥ የጠየቁ የግብርና ባለሙያ እንደተናገሩት ከሶማሌ ክልል በስተቀር በመላ አገሪቱ የግዳጅ የእርከን ስራ በመካሄድ ላይ ነው።

አርሶ አደሩ የእርከኑን ስራ በአወንታዊ መልክ እንዳልተቀበለው የገለጡት እኚሁ ሰራተኛ፣ የግዳጅ ስራው ዋና አላማ ህዝቡ ሌሎች ነገሮችን እንዳያስብ በስራ ለመወጠር ነው።

## ወያኔ ሆነ ብሎ በምግብ እህሎች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ መፍጠሩ ተጋለጠ

ለደሃው አንዳችም አዘኔታ የሌለው የዘራፊው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በምግብ እህሎች ላይ ዋጋ እንዲጨምር በማድረግ የድሃውን አጥንት እየጋጠ መሆኑ ተጋለጠ።

ሰሞኑን በተለይ በጤፍ እና የአንዳንድ የእህል ምርቶች ዋጋ የታየው ጭማሪ ሆነ ተብሎ የተደረገ ደባ መሆኑን ውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ። በዚህ የዘረፋ እቅድ ምክንያት በጤፍ ላይ በአማካይ 200 ብር የሚደርስ ከፍተኛ እና ያልተጠበቀ ድንገተኛ ጭማሪ ታይቷል።

በሰሜን ጎንደር ነዋሪ የሆኑ አንድ ሸማች የችግሩ ምንጭ የመንግስት አሰራር የፈጠረው ነው ይላሉ፤ የኑሮ ውድነቱ በደሀውና በመንግስት ሰራተኛው ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽኖ እየፈጠረ የህዝቡ ምሬትም ጎልቶ እየተሰማ ነው።

ለወትሮ እህል በሚረክስበት በየካቲት መጨረሻ ላይ ይህንን የመሰለ የዋጋ ጭማሪ ማምጣት የግፍ ግፍ ነዉ ያሉ ብዙዎች ናቸው። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የአድዋ ድልን ኩራታችን፤ በወያኔ መገዛት ውርደታችን ነው!!

የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም!!! የአድዋ ድል!!!

የአድዋ ድልን ዘንድሮ ለ116ኛ ጊዜ እናከብራለን። ይህች ቀን ለኢትዮጵያዊያን ታላቅ የክብር ቀን ናት። ይህች ቀን ከኢትዮጵያዊያንም አልፎ ለመላው አፍሪቃ ከዚያም አልፎ ለመላው የጥቁር ዘር ታላቅ እለት ናት። ዘርም ሆነ ቀለም ሳይመርጡ ለሰው ዘር እኩልነት ለሚታገሉ ሁሉ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ታላቅ ትርጉም አላት። በዚች እለት አባቶቻችንና እናቶቻችን ለራሳቸው ከፍ ያለ ክብር የሚሰጡ፤ የነፃነትን ትርጉም የተረዱ ነፃ ሰዎች መሆናቸውን አስመስክረዋል። በዚህ እለት ነፃነትና ክብር ለነጮችና ለሃብታሞች ብቻ የተሰጠ ሳይሆን ለሰው ልጅ ሁሉ የተሰጠ ፀጋ መሆኑን፤ ይህንን ለመፃረረ የሚነሳ ኃይልን በኃይል መመከት የተቀደሰ ተግባር መሆኑን አስመስክረዋል። በዚች እለት ልማትና ስልጣኔ ከነፃነት በላይ እንዳልሆኑ ይልቁንም ሰው ነፃነቱን ካጣ ስልጣኔም ሆነ ልማት ትርጉም የለሽ መሆናቸውን አባቶቻችንና እናቶቻችን ለመላው ዓለም ያስተማሩበት እለት ነው።

እንደሚታወቀው በወቅቱ የነበረው የጣሊያን መንግሥት ኢትዮጵያን "ሊያለማና ሊያሰለጥን" ቃል ገብቶ ነበር። ይህንን ለማድረግ አቅም ነበረው። ከወታደሮቹ ጋርም መንገድ ሰሪዎችንና ህንፃ ገንቢዎችን መላኩም እውነት ነው። ነገር ግን አባቶቻችንና እናቶቻችን "ጣልያን ነፃነታችንን ገፎ ከሚያመጣልን ልማትና ስልጣኔ ይልቅ ነፃነታችንና ክብራችን ተጠብቀው ብንደኸይ እንመርጣለን" በማለታቸው፤ ለዚህም የህይወት መስዕዋትነት ከፍለው ወራሪውን በመመከታቸው እነሆ እስከዛሬ ድረስ የመንፈስ ስንቅ የሆነንን የአድዋ ድልን አኖሩልን። ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያዊነታችን ከሚያኮሩን ነገሮች አንዱ የአድዋው ድል ነው። ኢትዮጵያ በአፍሪቃና በዓለም አደባባይ አንገትዋን ቀና እንድታደርግ የሚያደርጋት አንድ የታሪክ እሴትዋ የአድዋ ድል ነው። አገራችን የነፃነት አርማ ሆና እንድትታይ የአድዋው ድል ያበረከተው አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው።

የሚያሳዝነው፣ አያቶቻችን፣ አባቶቻችንና እናቶቻችን ባህር ተሻግረው ከመጡ ባዕድ ወራሪዎች ተከላክለው ያስረከቡንን አገር እኛ ለጥቂት የትግራይ ገዢ ጉጅሌ አባላት አስረክበን መቀመጣችን ነው። አያቶቻችን፣ አባቶቻችንና እናቶቻችን በዘመናቸው ኃያል የነበረውን የጣልያን ወራሪን መከቱ፤ እኛ ግን ከጉያችን የወጣውን ደካማውን የወያኔ ወራሪን መመከት አልቻልንም። አያቶቻችን፣ አባቶቻችንና እናቶቻችን እንደምን ይታዘቡን?!

ከአድዋ ጦርነት በፊትም ሆነ ከዚያ ብዙ አስርት ዓመታት በኋላ ጣልያን ኢትዮጵያን ሊገዛ ሲዘምት ልማትንና ስልጣኔን እየሰበከ ነበር። የጣልያን ገዢዎች

> *ለኢትዮጵያዊያን የሚያስፈልገውን የምናውቀው እኛ ነን። መንገድ እንሰራለን፤ ህንፃ እንገነባለን፤ አስኳላም እንከፍታለን። እናንተ ለጣሊያን ተገዙ። ለእናንተ የሚበጀውን እኛ እናደርጋለን። "እኛም ሰው ነን አትበሉ፤" አይደላችሁምና። "እኛ አገር አለን አትበሉ፤" አገር የላችሁምና!!! እኛ ያዘዝናችሁን ብቻ ፈጽሙ። እኛ ያዘዝናችሁን መፈፀም ለእናንተ ይበጃችኋል።*

ይሉ ነበር። ቀደምቶቻችን ይህን የጣልያን መደለያ አልተቀበሉም።

ዛሬ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የጣልያን ቅኝ ገዢዎች ሲሉን የነበረውን ቃል በቃል እየደገመልን ነው። አያቶቻችን ጣልያንን አሳፍረው ለራሳቸውም ለእኛም ኩራት ሆኑ። እኛስ? መለስ ዜናዊን አሳፍረን ለራሳችንና ለልጅ ልጆቻችን ኩራት እንሆናለን? ወይስ ዛሬ ያለንበትን ባርነት ላለማየት ዓይኖቻችንን ጨፍነን በአያቶቻችን ጀግንነት እየኮራን እንቀያለን?

ዘንድሮም እንደ አምናው የካቲት 23 ቀን የአድዋን ድል የምናከብረው በቀደምቶቻችን እየኮራን፤ በራሳችን ግን እያፈርን መሆኑ ነው። አያቶቻችን፣ በሃብትና በመሣሪያ እጅግ ከሚበልጣቸው የጣልያን ወራሪ ጋር ተዋግተው ያዳኗትን አገር እኛ ለባንዳ ልጆች አስረክበናታል። ቀደምቶቻችን ለእያንዳንዷ ጭብጥ አፈር ያልሞቱትን ያህል፣ ዛሬ ሰፋፊ ለም መሬቶቻችን ለጎረቤት ሀገር እጅ መንሻና ከሩቅ አገራት ለመጡ ቱጃሮች በብላሽ ሲታደሉ እያየን ዝምታን መርጠናል። ቀደምቶቻችን በውጭ አገር ዜጎች ለመገዛት ባለመፍቀዳቸው ስንኮራባቸው፤ እኛ ግን በኛው አገር ሰዎች እየረተገጥን፣ እየተዋረድን ነው።

እውን እኛ የእነዚያ ኩሩ ኢትዮጵያን የልጅ-ልጆች ነን ማለት ይቻለናልን? በእነሱ ተጋድሎ ለመኩራትስ መብት አለን?

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የዘንድሮን የየካቲት 23 ቀን የአድዋ ድል መታሰቢያ በዓል የሚያከብረው በጣምራ ስሜት ነው። በአንድ በኩል አባቶቻችንና እናቶቻችን ለነፃነትና ለክብር በነበራቸው ቀናዒነት ይኮራል። ግንቦት 7፣ አገራችንና ሰንደቅ ዓላማችንን ጠብቀውልን ላቆዩን አርበኞች ከፍተኛ ክብርና አድናቆት አለው። በሌላ በኩል ግን እነሱ በተጋድሎ ያስቀሯትን አገር ለባንዶች ማስረከባችን ያሳፍረዋል። አያቶቻችን ከባዕዳን መንጋጋ መንጭቀው ያዳኗትን አገር ከእኛው መሃል ለወጡ ባዕዳን አሳልፈን መሰጠታችን ያንገበግበዋል።

ግንቦት 7፡ ይህ ትውልድ ከደረሰበትን ታሪካዊ ውርደት መውጣት አለበት ብሎ በጽኑ ያምናል። መንገዱን አያቶቻችን ከዛሬ 116 ዓመት በፊት አሳይተውናል። መንገዱ አርበኝነት ነው፤ ተጋድሎ ነው፤ ትግል ነው።

የአያቶቻችን የልጅ ልጆች፤ የአባቶቻችንና የእናቶቻችን ልጆች ለመሆን እንድንችል ትግሉን እንቀላቀል፣ አለበለዚያ ግን በባርነት እየኖሩ በነሱ ተጋድሎ መኩራራት አሳፋሪ ነው ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ወያኔ በሆላንድ በዓባይ ግድብ ስም ገንዘብ ለማሰባሰብ ያደረገው ሙከራ ከኢትዮጵያውያን ብርቱ ተቃውሞ ገጠመው

ኢሳት እንደዘገበው ይኅው በወያኔው ቱባ ካድሬ በካሱ ኢላላ የተመራው ገንዘብ የመሰብሰብ ሙከራ ያልተሳካና ከሰላሳ የማይበልጡ ካድሬዎች ብቻ የተሳተፉበት ነበር።

የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!ጋዜጠኞች ይፈቱ! የመሬት ንጥቂያ በአስቸኳይ ይቁም! ሞት ለመለስ ዜናዊ! መለስና ግብረ አበሮቹ ለፍርድ ይቅረቡ! እና ምዕራባውያን መለስን መደገፍ አቁሙ! የሚሉና ለሌሎችንም መፈክሮች ያስተጋቡት ሰልፈኞች በስፍራው የደረሱት ሰላሳ ደቂቃ ቀድመው ነበር።

ከአዳራሹ ውጪ ስለነበረው የመረረ ተቃውሞ መረጃ የነበረው የስብሰባው መሪ በቤንሉክስ ሀገሮች የወያኔ አምባሳደር የሆነዉ ካሱ ኢላላ ስብሰባው ይጀመራል ከተባለበት ጊዜ አንድ ሰዓት ያህል ዘግይቶ ነበር ከስፍራው የደረሰው፤ይሁንና በዚህ ወቅት ሰልፈኞቹ መበተን ይቅርና የተቃውሞ ደምጻቸውን ይበልጥ ያሰሙበት ነበር።

በመሆኑም ተቃውሞው ከግምቱ ውጪ የሆነበት ካሱ በተሸበረ መንፈስ በደህንነቶች ታጅቦ በሶምሶማ በጓሮ በር ሹልክ ብሎ ለመግባት ተገዷል በወቅቱም በአዳራሹ የነበሩ ታዳሚዎች ከ 15 አይበልጡም ነበር።

ዶ/ር ካሱን በጓሮ በር ሲገባ ያዩት ኢትዮጵያውያንም ከኋላ ኋላው እየተከተሉ "ካሱ ባንዳ! ካሱ ሆዳም!" ሲሉት ተደምጠዋል።

እንደ ኢሳት ዘገባ የካሱን በስፍራው መገኘት ተከትሎከውጪ የኢትዮጵያውያኑ ተቃውሞ እያየለ በመምጣቱ በጣት የሚቆጠሩት ተሰብሳቢ ካድሬዎች መሰብሰብ ተስኗቸው ለረዥም ሰዓታት እየተፈራረቁ በመስኮት በማጮለቅ የተቃውሞ ሰልፈኞቹን ሲመለከቱ ተስተውለዋል።

በሁኔታው ከፍተኛ ብስጭት ያደረባቸው የስብሰባው አስተባባሪዎችም ለፖሊስ በመደወል ስብሰባቸው በጉልበተኞች እየተረበሸ መሆኑን በማመልከታቸው፤ በስፍራው የሆላንድ ፖሊስ ባልደረቦች ደረሱ።

ይሁንና ፖሊሶቹ በስፍራው ደርሰው ሁኔታውን ከተከታተሉ በሁዋላ "መስመራቸውን ጠብቀው መቃወም መብታቸው ነው"የሚል ምላሽ በመስጠት ክሱን ውድቅ አድርገውታል።

ኢትዮጵያውያኑ የተቃውሞ ድምፃቸውን አጠንክረው ማሰማታቸውን በመቀጠላቸው ወያኔ"ለዓባይ ግድብ "በሚል ገንዘብ ለማፈስ አቅዶት የነበረው ታላቅ ስብሰባ ከ 30 በማይበልጡ ካድሬዎች ሊካሄድ ግድ ሆኗል።

## ወያኔ ሆነ ብሎ በምግብ እህሎች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ መፍጠሩ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የስታትስቲክስ ባለሥልጣን በምግብ ምርቶች ላይ ታይቶ የነበረው የዋጋ ግሽበት እየቀነሰ እንደሆነ መግለጫ ባወጣበት ማግስት እንደ ጤፍ በመሣሰሉ ምርቶች ላይ ከፍ ያለ ጭማሪ መታዬቱ የወያኔ ስታትስቲክስ ቢሮ ሚያወጣቸዉ መረጃዎች ምን ያህል ከእውነት የተጣላ ስለመሆኑ ማስረጃ ነው ተብሏል።

የአሁኑ የዋጋ ጭማሪ ምንጭ ምን ሊሆን እንደሚችል የተጠየቁ ስማቸው እንዳይጠቀስ የጠየቁ ባለሙያ "ምክንያቱ የመለስ ዜናዊ ዘመዶችና አሽከሮች እህላቸውን ሰብስበው ለመሸጥ በመዘጋጀታቸው ሊሆን ይችላል" ብለዋል። እንደሚታወቀው የመለስ ዜናዊ ዘመዶችና አሽከሮች ሰፋፊ መሬቶችን ይዘው በሰፊ እያረሱና እያሳረሱ ነው። እነሱ እህል ወቅተው ሲሰበስቡ በውድ ዋጋ ለመሸጥ ሲሉ በሰው ሰራሽ አሻጥር ዋጋውን ሰማይ ይሰቅሉታል። እነሱ ለገንዘብ ሲሉ የማይሰሩት ወንጀል እንደሌለ ይኸው ባለሙያ ሲገልጹ "እህል ወደ ውጭ አገር ልከው ለማትረፍ ሲሉ በጉሊቶች ሳይቀር እየዞሩ እህል ይሸምታሉ" ብለዋል።

የመለስ ዜናዊ አረመኔያዊ አገዛዝ ሳይወገድ ረሃብ ከአገራችን ማጥፋት የማይቻል ስለመሆኑ አሁን አሁን ሰፊ ግንዛቤ እያገኘ የመጣ ጉዳይ ነው። የእነሱን ፎቅና የተንደላቀቀ ኑሮ እያሳዩን የአገሪቱ ኢኮኖሚ በየዓመቱ 11 በመቶ እያደገ ነው ማለታቸው በድሃው ቁስል ላይ እንጨት መስደድ ነው የሚሉ አሉ።

## የእሳት እራት
## ትውስታየ በውጭ ጉዳይ ሚንስቴር

(ክፍል 2 ካለፈው ሳምንት የቀጠለ)

ሀ ሁ ብየ ፊደል ቆጥሬ አ ቡ ጊዳንም ዘልቄ የእውቀቴን ልቀትና ጥልቀት ላሳፋ አስቤ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ገባሁ። ከዚህ የዘላለም የሰው ልጆች ማደጊያ ሥፍራ ከፍ ባለ ማእረግ ተመረቅሁ። ከዩንቨርስቲ ካገኘሁት እውቀት ላይ የአቶ ሃዱሽ ገ/እግዚአብሄር መልካም ፈቃድ ታክሎበት በውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ተቀጠርኩ። ሃዱሽ ገ/እግዚአብሄር ውጭ ጉዳይ የሚቀጠሩ ሰዎችን የጀርባ አጥንት/ታሪክ የሚያጠና ነው። ይህ ሰው በአቦጊዳ ላይ ሽፍቶ የኖረ ቢሆንም ትንጥየ "ጌታ" ሁኖ በሰዎች እድል ፈንታ ላይ ወሳኝ ሁኗል። ይቀጠር ያለው እየተቀጠረ አይቀጠር ያለው ደግሞ እየተከለከለ ለረዥም ግዜ በውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ውስጥ ሰርቷል። ይህ ሰው ክፉ አይደለም። ታዞ ሥራውን የሚሰራ በሰገባው የተገኘ ታማኝ አገልጋይ ነው። የጌቶቹን ትእዛዝ ተቀብሎ በራሱም ትንሽየ "ጌታ" ሆኖ እድል ፈንታቸውን የሚወስንላቸውን እጩ ተቀጣሪዎች የስም ዝርዝር ጽፎ የያዘበትን ዶሴ ይዞ ታች ላይ ሲል ከፍ ያለ የሥራ ኃላፊነት ያለውን ሰው ይመስል ነበር። ህወሃት አገሪቷን ከተቆጣጠረ ወዲህ ያገኘው የሞራል ልዕልና ካልሆነ በቀር በኑሮው የደላው ነገር ያለ አይመስልም። ህወሃቶች "አማራ ብርቱ ጠላትህ ነው አሮሞም ቢሆን አይተኛልህም" ብለው የነገሩትን ነውር ትምህርት አምኖ እርሱንም ትጥቅና ስንቁ አድርጎ የጀርባ አጥንት እያጠና በዜጎች እድል ፈንታ ላይ ውሳኔ ሰጪ በመሆኑ ደስ ብሎት የሚኖር ምስኪን ሰው ነበር። አሁን የት እንዳለ አላውቅም ምን አልባት የአንዱ አምባሰዳር ጠባቂ አድርገውት ይሆን ይሆናል። ምንአልባትም በአንዱ ኤምባሲ የጸጥታ ጉዳይ አማካሪ ሁኖ ይሆናል። በቦታውና በሰገባው የተገኘው አቶ ሃዱሽ ገ/እግዚአብሄር ይቅርና ዘውዱ የተባለው ነፍሰ ገዳይ በአማካሪ ማዕረግ ኬኒያ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ተመድቦ ብዙ ኢትዮጵያዊያንን ሲገድል አልከረመም ? አሁንስ ዱባይ ላይ የህወሃት ተወካይ ሆኖ "እየሰራ" አይደል ? በዱባይ *"ዜድ"* ቴሌቶን አቋቁሟል የሚባለውስ እርሱ አይደል ?የጸጥታ አማካሪ ማለት እንዲህ ያለውን ሥራ የሚሰራ ነው እንጂ ሌላ አይደለም። አቶ ሃዱሽ ግን ደከሟል ሩጦ ለመያዝ፤ አልሞ ለመቶኮስ፤ ጨብጦ ለመያዝ ጉልበቱ ያለው አይመስለኝም። የቀረው እድሜም ለንስሃ ከመሆን የሚዘል አይደለም።

ውጭ ጉዳይ ሚንስቴር ውስጥ መስራት ገንዘብ ምንስቴር ወይም ደግሞ ት/ት ምንስቴር ውስጥ እሰራለሁ እንደማለት ቀላል አይደለም። ውጭ ጉዳይ መሥራት ማለት በሁለት ስለታም ጥርሶች ውስጥ እንደመኖር ነው። የውጭ ሰዎች እንደ ህወሃት ካድሬ እየቆጠሩ በጎ ባልሆነ ዓይን ያዩሃል እዚህ ውስጥ ያሉት ደግሞ የድርጅታቸው አባል መሆንን ባለመውደድህ በጥርጣሬ እየተመለከቱህ በገዛ አገርህ ሃዘን በዝቶብህ ትኖራለህ።

አንድ የህወሃት ካድሬ በአንዲት ምሽት የሚያጠፉትን የምታክል ደመወዝ እየተከፈለኝ ለመስራት ተስማምቼ በውጭ ጉድያ መሥሪያ ቤት ስቀጠር በርቀት ያየሁትን ተስፋ እውን ለማድረግ አስቤ ነበር። ተስፋየን እውን ለማድረግ በጣም መራርና ከባድ የሆነውን ኑሮ ተያያዝኩት። ወሩ በገባ በሃያኛው ቀን ኪሴ ውስጥ የሚቀረው ገንዘብ ቁርስ፤ምሳና እራቴን ለመብላት አልበቃ እያለኝ ተቸገርኩ። ጠጪ አይደለውም። ገንዘብ እንዲሁ በቀላሉ የማባክንም ሰው አይደለውም። ብዙውን ግዜ ደግሞ እጾማለሁ። እንዲህም ሁኜ ከ600 ብር ተቆራርጦ የሚደርሰኝ 520 ብር ጨርሶ ከወሩ ጥግ አያደርሰኝም። ከወሩ ውስጥ አምስቱን ቀናት ራቴን ዳቦ በሙዝ እየጨረግድሁ አድራለሁ። አንዳንዴም አጋጣሚ ሆኖ ከደላኝ አቦካዶ ገዝቼ እርሱን በዳቦ ገምጬ ተመስገን ብየ እተኛለሁ። በእንቅልፍ ከመውደቄ በፊት ግን ውጭ ስመደብ ይሄ ሁሉ እንደሚቀየር ስለሚሰማኝ ሥራየን ብቻ በርትቼ መሥራት እንዳለብኝ ለራሴ ነግሬ ለጥ እላለሁ። ሲነጋም ተነስቼ ፊቴን ተጣጥቤ በእግሬ ወደ ብሮየ አዘግማለሁ። እግረ መንግዴን ግቢ ገብርኤል ጎራ እልና ጠበል እጠጣለሁ። እርሱ ቁርስ መሆኑ ነው። ጠበል ስጠጣ ለምን እንደሆነ አላውቅም ሳይርበኝ እስከ ምሳ ሰዓት እቆያለሁ። 11% ኢኮኖሚው አደገ በሚባልበት አገር ውስጥ አንድ የመንግስት ሰራተኛ በዚህ ሁኔታ ይኖራል።

እስኪ ዘወትር ኢኮኖሚያችን በ11% አድጓል እያለ የሚያደርቀኝና ከእኔው ጋር አንዲቷን ቢሮ ወደ ሚጋራኝ ግለሰብ እንሂድ።

"ተራራውን አንቀጥቅጬአለሁ" ከሚለው ህወሃት ከተሰኘው ደርጅት ጋር ከትግል ሜዳ ያልዋለ ነገር ግን ከከተማ ሁኜ ስረዳ ነበርኩ የሚል አንድ አባል አብሮኝ አለ። ይህ ሰው "የነጻነት ታጋዮች" ነን ባዮች አገሪቷን ከተቆጣጠሩ በኋላ በለስ ቀንቶት በሚያስገርም ፍጥነት ትልቅ ህንጻ አሠርቶ ለውጭ አገር ሰዎች አከራይቶት በየወሩ 42 ሺህ ብር ይሰበስባል። አትገረሙ። 42 ሺህ ብር ብዙ አይደለም። በእነዚህ ቡድኖች በዚያች አገር ላይ የሚፈጸሙ በጣም በጣም የሚያስደንቁ ነገሮች ሞልተዋል።

ይህ ሰው አለቃ የለውም። አለቃ ያለኝ እኔ ነኝ። እርሱ ደስ ባለው ሰዓት መኪናውን አስጓርቶ ልቡ ወደ መራው ይሄዳል ባሰኘው ሠዓት ደግሞ ይመለሳል። እኔ ከማን ጋር ሻይ እንደጠጣሁና የት እንደዋልኩ ፌርማቶሪ ተመድቦ መግቢያ መውጫየን ይከታተላል። እርሱና መሰሎቹ አሳዳጅ እኔ ተሰዳጅ ሁነን በኢትዮጵያችን እንኖራለን። ሁለት የተለያየን ዜጎች በኢትዮጵያ አለን። ኢትዮጵያ የሁላችንም አገር ብትሆንም እነርሱ ግን የሌላ ባእድ አገር የሚገዙ ይመስላቸዋል። እኔም ለእነርሱ እንደ ባእድ ነኝ።

የእነርሱ ላልሆነች አገር ደግሞ የሚያሳስባቸው ምንም ነገር የለም። እኔን የመሰሉ ብዙ ሚሊዮናት ሲራቡ፤ሲጠሙ ፤ሲታረዙ፤እነርሱ ይስቃሉ እንጂ ትንሽም ደንገጥ አይሉም። በበሉትና በጠጡት መጠን እነርሱ እድገታችን ነው የሚሉትን እየለኩት ያደርቁናል እንጂ የእለት ጉርሱን አጥቶ በየሜዳው ወድቆ የሚቀረው የአገሪቱ ዜጋ አይታያቸውም። ይህ እውነት ሲነገራቸው ጠላት ያደርጉሃል እንጂ አያዳምጡህም።

ይህ ሰው እንደፈለገ እየሆነ "ይህች ደግሞ ምን አላት" ብሎ የሚንቃትን የወር ደመወዙን ሳይቦዝን ይቀበላል። መቸስ የአገሪቷ ህግ እርሱን ለመሰሉት ሁሉ መጠቀሚያ እኔን ለመሰሉት ደግሞ መጠቂያ ሁኖ ተሰርቷል። በዚያች አገር እኔንና እርሱን እኩል የሚገዛ ህግ የለም። እርሱና መሰሎቹ ከህግ በታች ላለመሆን "ነፃ" ወጥተው ከህግ በላይ ሁነዋል። እርሱንና እኔን እኩል የሚገዛ ሥርዓት ቢሰራ ጥቅሙ ስለሚቀርበት እንዲያ ያለ ሥርዓት እንዲፈጠር ፈጽሞ አይፈልግም። እንዲህ ያለ ነገር የሚጠይቅ ካለም ወዲያውኑ በጠላትነት ይፈረጃል። አሸባሪም ይባልና የመከራ እንጀራን ይበላል የመከራ ጽዋንም ይጎነጫል።

ሰውየው የሥራ ደረጃው አንደኛ ጸሃፊ ነው። በውጭ ጉዳይ ሚንስቴር የሥራ እርከኖች ከምሩቅ አታሼ ጀምሮ አታሼ ፤ሶስተኛ ጸሃፊ፤ሁለተኛ ጸሃፊ፤አንደኛ ጸሃፊ ፤አማካሪ፤ምንስትር አማካሪ ከዚያ እድለኛ የሆነ ካተገኘም አምባሳደር ይሆናል። እነዚህን የውጭ ጉዳይ እረከኖች አልፎ በችሎታውና በልምዱ ለአምባሳደርነት ደረጃ የበቃ ሰው አሁን ባለው ውጭ ጉዳይ ሚንስትር ውስጥ የለም። በእርግጥ አምባሳደር ቆንጅት የምትባል አለች። እርሷ የጊዜው ፖለቲካ ገብቷትና ዓለማችን የደረሰችበትን የእድገት ደረጃ ተርዳታ አገራችንን ትጠቅማለች ተብላ የቆየች አይደለችም። ሴትየዋ ግዜ ተወስዶ የተተየቡ ደብዳቤዎችን "እዚህ ጋ ንጉሱ 'ሠ' ነው መግባት ያለበት እዚህ ጋ ደግሞ ዓይኑ 'ዓ' ነው መግባት ያለበት እያለች ለንጉሱ 'ሠ' እና ለዓይኑ 'ዓ' እያለች ደብዳቤዎችን ቀዶ ከመጣል በቀር ይሄ ነው የሚባል እውቀት የላትም።

ሌላ እውቀቷ ደግሞ "አባሳጆ እኮ ወሬኛ ነው። ጋዳፊ ባለጌ ነው። አለባሽር የዋህ ሰው ነው። ቻርሌስ ቴይለር የነጭ አሽከር አጨብርባሪ ነው" ማለትን ግን ተክናበታለች። ይህ ደግሞ ሃሜት ነው።

በሶስቱም ሥርዓት በዚያ መስሪያ ቤት ለመቆየት የቻለችው ሃሜተኛ እና አደር ባይ በመሆኗ እንጂ ለዲፕሎማሲ የሚሆን እውቀት ኑሯት አይደለም። እርሷ ሂሊናዋ ስለማይጠይቅ ለመልአክም ይሁን ለሰይጣን ለመስራት ልቧ ፈቃደኛ ነው። በንጉሱ ዘመን ዲፕሎማት ነበረች፤ መንጌ ንጉሱን ገድሎ ሲመጣ ደግሞ ከፍ ብላ አምባሳደርነትን ተቀብላ ኖረች፤ ህወሃት ደግሞ ደርግንም ኢትዮጵያንም አንድ ላይ በልቶ ሲመጣም እርሱን ተቀብላ ደርግን እያማች አብራ ቀጠለች። ህወሃት የአጼ ሃይለ ስላሴ ሃውልት በአፊሪካ አዳራሽ አያስፈልግም ሲል እርሷም አዎን አያሳፈልግም ብላ ኑሯዋን ትኖራለች። እርሷ አማራ ነች ቢሆንም ግን እነመለስ "አማራና ኤምፔሪያልዝም የትግሬ ቀንደኛ ጠላቶች ናቸው" ብለው የጻፍትን ሰነድ ያየችው አይመስለኝም። ምክንያቱም ማንበብና መጠየቅ እጣ ክፍሏ አይደሉም።

የትምህርት ደረጃዋን በተመለከተ ድሮ በንጉሱ ዘመን ከእንግሊዝ አገር በሴርትፊኬት ተመርቃለች። ከዚያ ልቃ ሂዳ ቀለም አልቆጠረችም።

ከእንግሊዝ አገር ሰርቲፊኬቷን ይዛ እንደተመለሰች እንዲህ የሚል ማመልከቻ ጻፈች፤

> *"ከእንግሊዝ አገር ያገኘሁት ሰርቲፊኬት ከኢትዮጵአያ ድግሪ ጋር የሚተካከል በመሆኑ በዲግሪ እንዲያዝልኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ"*

ይህ እንግዲህ ንጉሱ ሳይወርዱ የተጻፈ ማመልከቻ ነው። የንጉሱ ሹምም እውቀቷን ሳይሆን ጀርባዋን አይተው ቀጠሯት።

የስድስት ወር የምስክር ወረቀት እንደምን ሁኖ ድፍን አራት ዓመት ተለፍቶ ከሚገኝ ድግሪ ጋር እኩል ይሁንልኝ ተብሎ ይጠየቃል ?ለዚያውም በንጉሱ ዘመነ መንግስት። "ክብርት" አምባሳደር ቆንጅት ስነጊዮርጊስ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ካላት መልስ እንድትሰጥበት እጠይቃለሁ። አምባሳደሯ በህይወት ዘመኗ ትዳር አልያዘችም። አምባሳደር የሚል ቅጽል ባይኖራት ኑሮ ወ/ት ተብላ ትጠራ ነበር። እደለኛ ነች መደበቂያ ቅጽል ማንጠልጠልን ችላበታለች።

የወ/ሪት ቆንጂትስ ይሁን አስራ ሁለተኛን ጨርሳ እንግሊዝ አገር ሂዳ ጥቂት ተምራ ሰርቲፊኬት አምጥታለች ደግሞም ነጉሱ "ሠ" እና ዓይኑ "ዓ"ን ጠንቅቃ ለይታለች። በዘመነ ህወሃት ፌደል ቆጥረው መጨረሳቸው በውል ሳይለይ በህግ ማስትሬት ድግሪ የታደሉ ብዙ ከፍተኛ ባለስልጣናት ሞልተው ተርፈው የለም እንዴ ?አገሪቷስ የምትመራው እንዲህ የአገሪቷን የትምህርት ስርዓት በሚያፈርሱ ቡድኖች አይደለም እንዴ ? ለምሳሌ በአሁኑ ሰዓት በስዊድን የኢትዮጵያ ልዩ መልእክተኛ መብራት በየነን ማየት ይቻላል።

"ንግባኢኬ ሃበ ጥንተ ነገር"ይላል አንድ መጽሃፍ ወደ ቀድሞ ነገራችን እንመለስ ማለት ነው። (ክፍል 3 ሳምንት ይቀጥላል)

## በኢትዮጵያ ሙስናን ለማጥፋት ፍላጎት እንጂ የፖለቲካ ቁርጠኝነት የለም ሲል የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ መስራችና የፖለቲካ መሃንዲስ ስብሃት ነጋ ተናገረ

በከፋ ሙስና መጨማለቃቸው በሰፊው ከሚነገርላቸው አንዱ የሆነው አንጋፋው የህወሃት መስራችና የዘረኛ ፖለቲካው ርዕዮት አቀንቃኝ የሆነው ስብሃት ነጋ በኢትዮጵያ ሙስናን ለማጥፋት ፍላጎት እንጂ የፖለቲካ ቁርጠኝነት የለም፤ ዛሬ በአገሪቱ የሰፈነው ሰርቆትና ዘርፎ መብላት በህዝቡ ውስጥ ሰርጾ ባህል እየሆነ መጥቷል በማለት "የኢትዮጵያ ሰላምና ልማት የሚባለዉ የወያኔ ተቋም ከፍሬድሪክ ኤቨርት ስቲፍተንግ ጋር " ሙስና፣ልማትና ዴሞክራሲ" በሚል በጋራ ባዘጋጁት የውይይት ፕሮግራም ላይ ተናገረ።

ሙስናን ለመዋጋት ፍላጐት፣ ቀጥሎም የፖለቲካ ቁርጠኝነት፣ተግባርና ውጤት ያስፈልጋል ያለው ስብሃት አንዳንድ የሙስና ሀሜቶች ከሰባት ዓመት በላይ ሲወሩ ቆይተዋል፣ ምንም እርምጃ አልተወሰደም፤ ችግሩ በዚህ ከቀጠለ እየተቆለለ መጥቶ ፈንቅሎ ማውጣት የማይቻልበት ደረጃ ይደርሳል በማለት አክሏል።

በተጨማሪም በኢትዮጵያ በተጨባጭ ያለው ሙስናን ለማጥፋት ፍላጎት እንጂ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ብሎ ነገር የለም፤ ይኼ በሌለበት ተግባርም ውጤትም አይኖርም፤ ቁርጠኛ ሌባ አለ ቁርጠኛ ተዋጊ ግን የለም ሲል በውይይቱ ላይ የተሳተፉትን አስደምሞአል። በህወሃት ውስጥ ባለው ስልጣን፤ ፖሊሲ አውጪና አስፈጻሚ ሆኖ ሳለ ማንን ለመውቀስ ይህንን እደተናገረ ግልጽ ያልሆነላቸው ተሰብሳቢዎች ወያኔዎች ራሳቸው የፈጠሩትን ችግር በአደባባይ በማውገዝ ከሃላፊነት የመሸሽ የቆየ ልማዳቸው ነጸብራቅ ነው ብለውታል።

በሌላ በኩል ጸረ ሙስና ኮሚሽን ተብዬዉ፤ ከፍተኛ ባለስልጥናት የሚሳተፉበት "ግራንድ ኮራፕሽን" በአገሪቱ ውስጥ የለም ሲል ሙልጭ አድርጎ መካዱን ሪፖርተር የተባለው አፍቃሪ ወያኔ ጋዜጣ ገልጿል።

የሪፖርተርን ዘገባ መነሻ አድርጎ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አስተያየት ሰጪዎች ስብሃት ራሱ በሙስና የተጨማለቀ ሆኖ ይህንን ያለው ከነካችሁኝ እኔም የማውቀውን አወጣለሁ በሚል ራሱን የተከላከለ መስሎት ነው፤ ምናልባትም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሙስና እመቤት ከምትባለው የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ጋር መጋጨታቸው መነሻ ምክንያቱ ሊሆን ይችላል ሲሉ አብራርተዋል።

በሌላ በኩል ተልዕኮዬ ሙስናን መከላከልና ሙሰኞችን ለህግ ማቅረብ ነው እያለ የሚመጻደቀው የወያኔዉ ጸረ ሙስና ኮሚሽን የኢትዮጵያ ባለስልጣናት ሙስና ውስጥ የሉበትም ሙስና የሚፈጸመው በዝቅተኛ ደረጃ ነው ማለቱ የሚያስተዛዝብ ብሎም የሚያሳዝን ነው ብለውታል።

ምንም እንኳን የራሱ ዓላማ ኖሮት ስብሃት ትክክለኛውን ነገር ቢናገርም ህዝቡን ያለ ዓመሉ ሰርቆና ዘርፎ መብላት ባህሉ ሆኗል ሲል በመኮነን ጥላቻውን በግልጽ አሳይቷል።

ሰርቆና ዘርፎ መብላት ከጫካ ጀምሮ አብሮት የኖረ የወያኔ ባህል እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ ባህል አይደለም ያሉት አስተያየት ሰጪዎች የህዝብን ሀብት ወደ ውጪ ማሸሽ፣ በዘመድ መስራት፣ በመንግስት ሀብትና ንብረት ያለአግባብ መጠቀም ወዘተ. የዘረኛው የወያኔ ስርዓት ዋነኛ መገለጫዎች የሆኑ የሙስና ተግባራት ናቸው ብለዋል።

በመጨረሻም ከተወያዮች «ፈሪሐ እግዚአብሔር ጠፍቶ ነው፤ ሙስና እየተስፋፋ ያለው» በሚል ለተሰጠው አስተያየት ስብሐት ሲመልስ፣ «ድሃ ነው ሃይማኖቱን ይዞ የተቀመጠው እንጂ አለቃው ምን ሃይማኖት አለው? አሁንስ ቢሆን በሃይማኖት አካባቢስ የምንሰማው ስንት ጉድ አለ አይደለም እንዴ? ሃይማኖት ሙስናን አያጠፋም:: አጥፍቶም አያውቅም:: ትልቁ ሙስና እዚያ ነው ያለው፤» ብሏል::

## አዲስ አበባ ውስጥ የመጠጥ ውሃ ችግር መባባሱ ተገለፀ

የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የመጠጥ ውሃ ችግር በከፍተኛ ሁኔታ መባባሱን የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን ገለፀ። ቀድሞ የመጠጥ ውሃ ችግር ያልነበረባቸው እንደ ቦሌና ገርጂ የመሳሰሉ አካባቢዎች ሳይቀሩ የመጠጥ ውሃ ካጡ ሳምንታት ተቆጥረዋል። ካዛንቺስ፣ አራት ኪሎ፣ ሽሮ ሜዳ ከቦቴዎች ውሃ ለመግዛት ረዣዥም ወረፋዎችን መጠበቅ ግዴታ ሆኗል። የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ውሃ በጀሪካንና በባልዲ መግዛት እየተገደዱ ነው። ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው የአዲስ አበባ ነዋሪዎች "ኑሮ ከድጡ ወደ ማጡ ሆኖብናል" ብለዋል።

የመብራት ፈረቃም ቢሆን እስካሁን መፍትሄ ያላገኘ ጉዳይ ነው። የወያኔ ሹማምንት አገሩን ሁሉ የሚያለማ መስኖ የተዘረጋ እና ለአፍሪቃ የሚበቃ መብራት የሚያመርቱ ግድቦች መገንባታቸውን የሚሰብኩ ቢሆንም ነዋሪዎች ግን 40 ሻማ አምፖላቸውን የሚያበራላቸው የኤክትሪክ ጉልበት እና ለመጠጥና ለምግብ ማብሰያ የሚሆን ውሃ እንኳን ማግኘት አልቻሉም።

በመብራት መጥፋት ምክንያት የዘረኛው መለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን ጄኔሬተሮችን እያስመጣች በመሸጥ ከፍ ያለ ሃብት ማካበቷ ይታወቃል። የአዲስ አበባ ነዋሪዎች "በውሃ መጥፋት የሚጠቀሙ እነማናቸው?" በማለት እየጠየቁ ነው። አንዲት እናት ለዘጋቢያችን "ወያኔዎች የሚገዛቸው ቢያገኙ ኖሮ እኛን ገበያ አውጥቶ ይሸጡን ነበር" ብለውታል።

ዘጋቢያችንም ወያኔ እሳቸው እንዳሉት ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ሰውን ሲሸጥ እንደነበር፤ ወደ አረብ አገራት የሚጋዙ እህቶቻችንና በጉዲፈቻ የሚሰጡ ህፃናትን በማስረጃነት በማንሳት ሲያስረዳቸው ጭንቅላታቸውን ይዘው "እግዚኦ ምነው በአገሩ ወንድ ጠፋ? ልጆቻችን ምን እስከንሆን ነው የምትጠብቁት?" ሲሉ ማማረራቸውን ገልጿል።

እንደዘጋቢያችን ግምገማ አገሪቷ በችግሮች ብዛትና ጥልቀት ልትፈነዳ የደረሰች ፊኛ ሆናለች።

የአብደላ ሳልህ በየመን ውስጥ መቆየት በአዲሱ ፕሬዝዳንት አብድራቡ መንሱር ሃዲ, እንዲሁም የስልጣን ሽግግሩን ባስፈፀሙት አለም አቀፍ ሽምጋዮች እና በየመን ህዝብ በኩል ተቀባይነት አላገኘም። የየመን ወጣቶች አሊ ሳላህ ለፍርድ ይቅረብ እያሉ ነው።

በዚህ ጭንቀት ነው አሊ አብደላ ሳላህ መለስ ጉያ ውስጥ መደበቅን የመረጠው። ለአሊ አብዳላ ሳልህ ከአዲስ አበባ ወጣ ብሎ የመኖሪያ ቪላ እንደተዘጋጀላቸዉና የቤት እቃዎቻቸዉ ወደ ኢትዮጵያ በመጓጓዝ ላይ እንዳለም ለማወቅ ተችሏል።

መለስ ራሱ በኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ሲወድቅ የአሊ አብደላ ሳልህ እጣ ፈንታ ምን እንደሚሆን መገመት አስቸጋሪ ነው። እንግዳ ተቀባይነት የምንኮራበት ባህላችን ቢሆንም እንኳን የንፁሃንን ደም ያፈሰሱ አምባገነኖችን ተቀብሎ ማስተናገድና በህዝብ የተተፉ አምባገነኖች መሸሸጊያ መሆን ወንጀል ነው። የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ አሊ አብደላ ሳልህን ለመቀበል የፈቀደው የገንዘብ ጥቅም የሚያገኝበት በመሆኑ ነው የሚሉ አስተያየቶች እየተሰጡ ነው።

## ጥምረት ለነጻነት፣ ለእኩልነትና ለፍትህ ከሚያዘጋጃቸው ስብሰባዎች መካከል ሁለተኛው በሂውስተን ቴክሳስ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የኦሮሞ ህዝብ ነጻ ሊወጣ የሚችለው ከኦሮሞ ጋር ተቀላቅሎ የሚኖረውና ከኦሮሞ ክልል ውጪ ያለው አጠቃላይ ህዝባችን ነጻ ሲወጣ ብቻ ነው ያሉት የኦነግ አመራር አቶ አዴሳ ቦሩ፤ ድርጅታቸው አሁን የወሰደውን አቋም ለማጥላላት በተለይም ግንቦት 7 በፈጠረው ተጽዕኖ ነው ብለው የሚያስወሩ ሃይሎች የኦሮሞን ህዝብ ችግርና አገሪቱ በአጠቃላይ የገባችበትን ፈተና ለመረዳት ያልፈለጉ ናቸው ብለዋል።

ካረጀና ካፈጀ የፖለቲካ አስተሳሰብ ወጥቶ አንድ እርምጃ መራመድ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን የግድ ነው የሚሉት አቶ አዴሳ አዲሱ የኦነግ አቋም ሁሉንም ኢትዮጵያዊ አቅፎ የሚይዝ እንደሆነና ፍትህና እኩልነት የሰፈነባት ፤ በህዝቦች ፍላጎት ላይ የተመሰረተች አዲስቷን ኢትዮጵያ መገንባት፣ የብሄር ብሄረሰቦችንና የግለሰቦችን መብት ማስከበር፣ ኦሮሚያ የአዲስቷ የፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ አካል ማድረግ፣ የኦሮምኛ ቋንቋ ከአማርኛ ቋንቋ ጋር እኩል የስራ ቋንቋ እንዲሆን ማድረግና የህግ የበላይነት በአገሪቱ እንዲሰፍን መታገል የሁላችንም የጋራ ሃላፊነት ነው ብለዋል።

ተዋቂው አርቲስት ታማኝ በየነ በበኩሉ የመለስ አገዛዝ በዘረኝነቱ ምክንያት ባለፉት 20 አመታት ከድጡ ወደ ማጡ እየተጓዘ መሆኑን አመልክቷል።

አርቲስ ታማኝ ኢትዮጵያ ውስጥ ነጻነት ካለ የተለያዩ ማህበረሰቦች አመለካካታቸውን፣ እምነታቸውን እና ራዕያቸውን ይዘው ተፈቃቅረው ሊኖሩ እንደሚችሉ ታሪካዊ ማስረጃዎችን እያጣቀሰ ገለጣ አድርጓል።

በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ ከፍተኛ የስልጣን እርከኖች እና በውጭ አገር ባሉ ኤምባሲዎች ከፍተኛውን ቦታ የሚይዙት የህወሀት ካድሬዎች መሆናቸው አገሪቱ የገባችበትን ዝቅጠት ያሳያል ሲልም አርቲስት ታማኝ አክሎ ገልጧል።

የተወካዮቹ ንግግር እንዳበቃ ከቤቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበው ተሰብሳቢውን እጅግ ያረካና ያስደሰተ ምላሽ በመስጠት ስብሰባው ተጠናቆአል።

በተመሳሳይ ዕለት በካሊፎርኒያ ግዛት በሳን ጆሴ አቶ ኤፍሬም ማደቦ የጥምረት ስራ አስፈጻሚ አባልና አቶ አሚኑ ጂንዲ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ዋና ጸሃፊ ተገኝተው ተመሳሳይ መግለጫ ሰጥተዋል።

## የሙስሊም ማኅበረሰብ ያቀረባቸው የመብት ጥያቄዎች . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮችም የኢትዮጵያን ሙስሊሞች የመብት ጥያቄዎችን የሚደግፉ መሆኑን ዘጋቢያችን በአዲስ አበባ ከተማ በመዘዋወር ያሰባሰበው መረጃ ያመለክታል። አንዳንድ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች "ወያኔ እስላምና ክርስቲያንን ለማጋጨት ያልቆፈረው ድንጋይ የለም። አሁን ደግሞ እስላምን ከእስላም ጋር እያጋጨ ነው" በማለት መማረራቸው ዘጋቢያችን የላከልን ዜና ይገልፃል።

ባለፈው ሳምንት ግንቦት 7 "የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄዎች የሁላችንም ናቸው!!!!" የሚል መግለጫ ማውጣቱ ይታወሳል።


### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።